## በእምነት መንካት

### ሰው እምነቱ እንዲሰራ ለማድረግ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ድርጊቶችን ስለ መጠቀም መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የወንጌል አገልጋዮች ላይ በአማኙ ህዝብ የተለያዩ ትችቶች ሲቀርቡ ይታያል፡፡ የሚቀርቡት ትችቶች አንዳንዶቹ ተገቢ፣ ሌሎቹ ደግም ተገቢ ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተገቢ ትችቶችም ቢሆኑ መቅረብ ባለባቸው አግባብ ካልቀረቡ በተለይ በወንጌል ባላመኑት ላይ ወደ ጌታ እንዳይመጡ አሉታዊ ተጽዕኖ በማድረግ በጌታ ኢየሱስ ከማመን ሊያርቃቸው ስለሚችል እጅግ አስፈላጊ ያልሆኑ ትችቶችን በማህበራዊ ሚዲያዎች ከማሰራጨት ተቆጥቦ በቤተ-ክርስቲያናት የውስጥ ግንኙነት አሰራር መርህ መሰረት ቢከናወን የተሻለ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡

የተለያዩ የወንጌል አገልጋዮች ከሚተቹባቸው ጉዳዮች አንዱ አገልግሎት በሚያከናውኑበት ወቅት የተለያዩ እንደ መሃረብ፣ ውሃ፣ ዘይት የመሳሰሉ ቁሳቁሶች ይጠቀማሉ የሚል ነው፡፡

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በሰማይና በምድር ያሉ የሚታዩና የማይታዩ ፍጥረታት የፈጠረው ቃል በመናገር ነው፡፡ አሁንም ቃል በመናገር ታላላቅ ድንቆችንና ታምራዊ ሥራዎችን ይሰራል፡፡ ደግሞም እንዲህ ሲል ተናግሯል፡-

ኢሳ 55፥11፣ "ከአፌ የሚወጣውም ቃሌ፣ በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤ ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፤ የተላከበትንም ዓላማ ይፈጽማል…።"

እኛም አምነን ከእርሱ ኀሳብ ጋር የሚስማማውን ቃል ብንናገር የምንፈልጋቸው ነገሮች እንደ ሚሆኑልን አምላካችን ያስረዳናል፡፡

ማቴ 21፥21፣ "ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ፣ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ተራራ፣ 'ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ' ብትሉት እንኳ ይሆናል፤"

እግዚአብሔር ቃል በመናገር የፈለገውን ነገር ሁሉ እንደ ሚያስገኝ እኛም የምንናገረው ከእርሱ የሆነ የእምነት ቃል እንደ ሚሰራ በማመን ተግባራዊ ብናደርገው የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ እናገኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን እግዚአብሔር የሚለንን ነገር አምነን በመቀበል መለማመድ ቀላል አድርገን ስለ ማናየው የእምነታችን ማስተላለፊያ በመሆን እንዲረዱን አንዳንድ ቁሳቁሶችን እንድንጠቀም ይፈቅዳል፡፡

ለዚህ ጉልህ ምሳሌ የሚሆነን እግዚአብሔር ሙሴን ለአገልሎት በጠራው ጊዜ እርሱን ያስተማረበት ሂደት ነው፡፡ ከ ዘጸ 3፡7-16-17-22 ባለው ስፍራ እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘው ሄደህ ያልኩህን በመናገር የእስራኤልን ሕዝብ ነጻ የማውጣት ስራ ጀምር የሚል ነበር፡፡ ሙሴ ይህን አምኖ በመቀበል መሄድ ሲከብደው በምዕራፍ 4፡1-13 ላይ በትሩን ተጠቅሞ አንዳንድ ተአምራዊ ስራዎች እንዲሰራ አደረገው፡፡ አሁንም ሙሴ እግዚአብሔር የተናገረው ሁሉ አምኖ በመቀበል ስራ መጀመር ባለ መፈለጉ እግዚአብሔር ተቆጣው፣ ዘጸ 4፡14፡፡ ስለዚህ የእምነት ቃል ከመናገር በተጨማሪ እምነታችንን ከመንፈሳችን በማውጣት ስራ ላይ ለማዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱና ያልተጠቀሱ አንዳንድ ቁሳቁሶች መጠቀም የሚቻል መሆኑን ነው፡፡

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ሁልጊዜ አጠገባችን ቢኖርም ስለማናየው በስሜት ሕዋሶቻችን አንገናኘውም፡፡ ከእርሱ ጋር መገናኘት የመንችለው በእምነት ነው፡፡ እምነት እግዚአብሔርን የምንነካበት እጅ ነው፡፡ እጅ ደግሞ ካልተዘረጋ አጠገባችን ያለ ነገርን አይነካም፡፡ በእምነት ሆነን የምናደርጋቸውና የምንናገራቸው ነገሮች እግዚአብሔርን ለመንካት እጃችንን እንደ መዘርጋት ሆነው ይሰራሉ፡፡ እምነት በልባችን ሞልቶ ሳለ እግዚአብሔርን ሳንነካበት ዝም ካልነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ለኛ የሚያስፈልገን ነገር የሚያስገኝ ኃይል ስለማይወጣ ምንም ውጤት አያስገኝም፡፡ ይሄ እምነት ውስን በሆነው ሰውና በማይወሰነው እግዚአብሔር መካከል እንደሚያገናኝ ሽቦ አድርገን ለመጠቀም በእምነት ጌታን የመንኪያ መንገዶችን (ሜተድስ) እንጠቀማለን፡፡ እምነት ከልባችን ለማውጣት የተለያየ ድርጊት መፈጸም/እርምጃ መውሰድ አለብን ማለት ነው፡፡ ያለን እምነት መጠን ከፍታና ዝቅታ ሳይሆን ባለን የስናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ተጠቅመን ባለ መጠራጠር የምንፈጽመው ድርጊት ነው ልዩነት የሚያመጣው፡፡

አጠር ያለ ሽቦ ጋር የተያያዘ የአምፖል ማቀፊያ፣ አምፖል ቢደረግበትም የኤሌክትሪክ ኃይል ካለው ሶኬት ጋር ካልተገናኘ አምፖሉ አይበራም፡፡ እንዲበራ ከተፈለገ ከኃይል ምንጭ ጋር ከተያያዘ ሶኬት ማገናኘት/ማነካካት ያስፈልጋል፡፡ የሰውም እምነት ከአማኙ ወጥቶ ከእግዚአብሔር ጋር ካልተገናኘ የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት የሚችል ኃይል ከእግዚአብሔር ስለ ማይወጣ ሰው የሚያሰፈልገው ውጤት አያገኝም፡፡

ከመንፈሳችን ውስጥ እምነትን አፍኖ በመያዝ ፈንታ በመልቀቅ ለማውጣትና እግዚአብሔርን ለመንካት እንዲያስችለን የምናደርጋቸው ነገሮች ስናደርግ ያኔ ከእግዚአብሔር ጋር መነካካት ይሆናል፡፡ በዚያኑ ጊዜ ከእግዚአብሔርም የጠየቅነውን ጉዳይ የሚያስገኝ ኃይል ይወጣና የፈለግነው መፍትሔ/በረከት እናገኛለን፡፡

ምሳሌ ለመጥቀስ፡- ማር 5፡27-32፣ አስራ ሁለት ዓመታት ሙሉ ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት የጌታን ልብስ ጫፍ ብነካ እንኳ እድናለሁ ብላ አመነች፡፡ በልቧ የነበረው እምነት ልብሱን በመንካት ስታወጣ የሚፈሰው ደሟ ወዲያውኑ ቆመ፡፡ ወዲያውኑ ኢየሱስ ኃይል ከእርሱ እንደ ወጣ አውቆ፣ "ማነው ልብሴን የነካው አለ፡፡" የሚፈውሳት ኃይል ከኢየሱስ ወጥቶ የእርሷን የታመመ የሰውነት ክፍል ስለነካ ወዲያው ተፈወሰች፡፡ እርሷ የኢየሱስን ልብስ ጫፍ ስትነካ እምነቷ ወጣና ኢየሱስን ነካ፡፡ በዚህ ጊዜ እርሷንም የሚፈውሳት ኃይል የወጣው ከልብሱ ሳይሆን ከጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ስለዚህ የጌታ ኢየሱስ ልብስ ጫፍ ያገለገላት ከልቧ እምነቷን ለማውጣት እንደ መገልገያ ዘዴ በመሆን ነው፡፡

ሌላው ምሳሌ ያዕ 5፡14-16 "ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። [15] በእምነት የቀረበ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈውሰዋል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤ ኀጢአትም ሠርቶ ከሆነ፣ ይቅር ይባላል። …፤" ይላል፤

የታመመውን ሰው የሚፈውሰው በእምነት የቀረበ ጸሎት የሚያስገኘው የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ ዘይት መቀባት ግን እምነትን ለማስተላለፍ እንዲያግዝ ጥቅም ላይ ውሏል ማለት ነው፡፤

እምነት ከውስጥ ሰውነታችን በማውጣት እግዚአብሔርን የምንነካባቸው መንገዶች የመነካኪያ፣ ወይም እምነትን ሥራ ላይ የምናውልባቸው መንገዶች ልንላቸው እንላቸዋለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ እምነትን ስራ ላይ የማዋያ መንገዶች በ3 ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡-

1. እግዚአብሔር ራሱ የሰጣቸው/የሚሰጣቸው/የሚያሳያቸው በቋሚነት/ለሁል ጊዜ የሚሰሩ ነገሮች፡-
   እግዚአብሔር የእለት ተእለት ኑሯችን መመሪያ እንዲሆነን በቅዱስ ቃሉ የተገለጸው ፈቃዱ ወይም ትዕዛዛቱ በእምነት መተግበር፡፡ ያዕ 2፡26፣ "ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ይለዋል፤
   እግዚአብሔር በቃሉ አድርጉ የሚላቸው ነገሮች ማድረግ ዋናው እግዚአብሔርን በእምነት የመንኪያ፣ ወይም ወደ እርሱ ቀርቦ የመገናኛ መንገድ ነው፡፡ ሌላው ምሳሌ እግዚአብሔር ድምጹን በማሰማት የሚናገረውም ነገር ሰምቶ በማመን ተግባር ላይ ማዋል ነው፡፡ የተጻፈው ቃሉና ድምጽ በማሰማት የሚናገረው ቃሉ መተግበር ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ልዩ በረከቶችን ያስገኛል፡፡
2. እግዚአብሔር በአንድ በጊዜ በተወሰነ ወቅት ታምራዊ ኃይሉን ሊገልጥ ሲል አድርጉ የሚላቸው (የሚያሳያቸው) ነገሮች፡-
   **ለምሳሌ ሙሴን**፡- በትርህን ጣል/በትርህን በእጅህ ይዘህ ዘርጋ፣ እጅህን በብብትህ እድርግ/ከብብትህ አውጣ፣ ከአባይ ወንዝ ውሀ ቀድተህ በፈርዖን ፊት አፍስስ፣ የምድርን ትቢያ በበትርህ ምታ- (ተናካሽ ዝንብ ወጣ፣) ከምድጃ እፍኝ አፈር ወስደህ በአየር በትነው- (እባጭ አስከተለ፣) እጅህን ወደ ሰማይ አንሳ- (በረዶ መቅሰፍት ሆነ፣ ) እጅህን በግብጽ አገር ላይ ዘርጋ- (የአንበጣ መንጋ ምድሪቱን ወረረ፣) የመሳሰሉ ነገሮችን ተናግሮታል፡፡ በዚህ ስፍራ የተለያዩ ቁሳቁሶች እግዚአብሔር እምዲጠቀም ያደረገው ሙሴ እምነቱን እንዲያወጣ ብቻ ሳይሆን በተለይ በዘጸ ምዕራፍ 3 ላይ ሙሴ እግዚአብሔር የተናገረውን ለማመን እንዲያግዘው ጭምር ነበር፡፡
   ዘሁ 20፡77-11፣ በኮሬብ አጠገብ ባለው ዓለት ቃል ተናግሮ ውሃ ለህዝቡ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ለሙሴ ቢነግረውም እርሱ ግን ከዚያ በፊት ደጋግሞ መጠቀም በለመደው መሰረት በበትሩ ዓለቱን መታ፡፡
   ዘጸ 17፡8-13፣ ከአማሌቃውያን ጋር ውጊያ ሲደረግ ሙሴ እጆቹን ወደ ላይ በሚያነሳበት ጊዜ እስራኤላዊየን ያሸንፉ ነበር፣ እጆቹን ባወረደ ጊዜ ግን አማሌቃውያን ድል ያደርጉ ነበር፡፡

ኢያ 3፥13፣ "የምድርን ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙት ካህናት ገና እግራቸውን በዮርዳኖስ ውሃ ውስጥ እንዳስገቡ፣ ቊልቊል የሚወርደው ውሃ ወዲያውኑ ይቋረጣል፤ እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል።"

ኢያ 3፡15-16፣ ወቅቱም የመከር ጊዜ በመሆኑ፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ነበር፤ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በደረሱ ጊዜ እግራቸው ውሃውን እንደ ነካ፣ [16] ከላይ የሚወርደው ውሃ ቆመ፤ በጻርታን አጠገብ "አዳም" ተብላ እስከምትጠራው ሩቅ ከተማ ድረስ በመከማቸት እንደ ክምር ተቈለለ፤ ቊልቊል ወደ ዓረባ ጨው ባሕር የሚወርደውም ውሃ ፈጽሞ ተቋረጠ፤ ሕዝቡም ከኢያሪኮ ትይዩ ባለው አቅጣጫ ተሻገሩ።

ኢ.ያ 3፥17፣ “የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናትም፣ ሕዝቡ ሁሉ ማለት እስራኤል በሙሉ ፈጽመው እስኪሻገሩ ድረስ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በደረቁ ምድር ላይ ቀጥ ብለው ቆመው ነበር።”

ኢ.ያ 4፥18፣ “ካህናቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ተሸክመው ከውሃው በመውጣት እግራቸው ደረቁን መሬት ልክ ሲነካ የዮርዳኖስ ውሃ ወደ ስፍራው ተመለሰ፤ እንደ ቀድሞው ሁሉ ሞልቶ በዳሩ ሁሉ ይፈስ ጀመር። (ከላይ በተጠቀሱት ሁሉ የቃል ኪዳኑ ታቦትና የፈጸሙት ድርጊት እንደ እምነት ማውጫ ዘዴ ሆነው አገልግለዋል፤)

**ኢ.ያ 6፡2-5፣ ለኢ.ያሱም** በኢ.ያሪኮ ከተማ ዙሪያ ለ6 ቀናት እንዲዞሩ፣ በ7ኛው ቀን ሰባት ጊዜ ኢ.ያሪኮ ከተማን እንዲዞሩ፣ መለከት እንዲነፉና፣ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲጮሁ… ነግሮታል፡፡

ኢ.ያ 10፡12-13፣ እግዚአብሔር አሞራውያንን ለእስራኤል አሳልፎ በሰጠባት ዕለት፣ ኢ.ያሱ እግዚአብሔርን በእስራኤል ፊት እንዲህ አለው፤ “ፀሓይ ሆይ፤ በገባዖን ላይ ቁሚ፤ ጨረቃም ሆይ፤ በኤሎን ሸለቆ ላይ ቀጥ በዪ፤ [13] ስለዚህ ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪበቀል ድረስ፣ ፀሓይ ባለችበት ቆመች፤ ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም። ይህም በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። ፀሓይ በሰማዩ መካከል ቆመች፤ ለመጥለቅም ሙሉ ቀን ፈጀባት። (በዚህ ጊዜ ግን ካህኑ ኢ.ያሱ እምነቱን ሥራ ላይ ያዋለው ቃል በመናገር ነው)

> ዘፍ 31፡10-12 ያዕቆብ በጎችና ፍየሎችን የሚያጠቁት አውራዎች ዝንጉርጉር መሆናቸውን በህልሙ የእግዚአብሔር መልአክ ስላሳየው በእመነት ዝንጉርጉር በትር በጎቹ ውኃ በሚጠጡበት ስፍራ አኖረ፡፡

3. እግዚአብሔር ራሱ ባይሰጣቸውም የእግዚአብሐር ሰዎች የተለያዩ ቁሳቁሶች እምነታቸውን ስራ ላይ ለማዋል ተጠቅመዋል፡- **ጌዴዎን**፡- መሳ 6፡16፣19-20 ማሰሮ ይዘው ሰበሩ፣ ችቦና መለከት ያዙ፣
   **ነብዩ ኤልሳ፡-** 2ነገ 2፡19-22፣ ማሰሮና ጨው እምጡልኝ ብሎ በኢ.ያሪኮ ምንጭ ጨመረው፣ ውሃውም ተፈወሰ፡፡ 2ነገ 4፡38-41 የሚገድል መርዝ በነበረው ምንቸት ዱቄት ጨምሮ ፈወሰው፣ 2ነገ 6፡1-6 የእንጨት ቅርንጫፍ ቁራጭ በውሀ ሲጥለው ሰምጦ የነበረው መጥረቢ.ያ ተንሳፈፈ፣ 2ነገ 5፡1-14 ንዕማንን በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ታጠብ አለው፤ እንዳለውም ታጥቦ ከለምጹ ነጻ፡፡ ነብዩ ኢ.ሳያስ ንጉሱ ሕዝቅያስን ለመፈወስ ትኩስ የበለስ ጥፍጥፍ ተዘጋጅቶ በእባጩ ላይ ሲደርጉለት መፈወሱ 2ነገ 20፡7፡፡

በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዘይት መቀባት፣ ሥዕለት ለእግዚአብሔር መሳል … ወዘተ ጥቅም ላይ ውለዋል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ የሚታይ ለእግዚአብሔር ስዕለት የተሳለ የመጀመሪያው ሰው የይስሃቅ ልጅ ያዕቆብ ነው፡፡ ያዕ 28፡20-22

ማቴ 14፡35-36፣ ሰዎች የጌታ ኢየሱስ የልብሱ ጫፍ ለመንካት እየለመኑ በመንካት ይፈወሱ ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ የእውሩን ዓይን ጭቃ ቀብቶ፣ ሂደህ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፡ ፡ ሰውየውም ሂዶ ታጠበ፣ እያየም ተመለሰ፡፡

ጌታ ኢየሱስ በ ማር 7፡33፣ 8፡23፣ ዮሐ 9፡6፣ ላይ ምራቁን የታመሙትን ሰዎች በመቀባት /በማስነካት/ እንዲፈወሱ አድረጓል፡፡

ሐሥ 5፡15-16፣ የሐዋሪያው ጴጥሮስ ጥላ እንዲያርፍባቸው ህመምተኞች መንገድ ዳር የስቀምጡ ነበር፣

ሐሥ 19፡11-12 የጳውሎስ ሰውነት የነካው መሀረብና ጨርቅ ለፈውስና አጋንንት ለማውጣት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን እጅን መጫን፣ ማር 16፡18፣ የእምነት ቃል መናገር ሐሥ 3፡6፣ እጅ በማንሳት መዘርጋት፣ ማቴ 12፡13፣ አገልጋይ እግር ስር መደፋት ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ሉቃ 8፡47፡፡

ያዕ 5፡14-15፣ ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ-ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡ የእምነት ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሳዋል፤ ኃጢአትም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል፡፡

ጌታ ኢየሱስ አልኣዛር ወደ ተቀበረበት ቦታ ሂዶ ዝም ብሎ ቆሞ ስላየ ሳይሆን መቃብሩን ካስከፈተ በኋላ የእምነት ቃል ስለ ተናገረ ነው አልዓዛር ከሞት የተነሳው፡፡ ማር 11፡20-23 “.... ማንም ይህን ተራራ ፣ ተነቅለህ ወደ ባህር ተወርወር ቢለውና ይህንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል፡፡” በልብ አምነው ካልተናገሩ/ካልጸለዩ ወይም ወይም ከላይ የተጠቀሱት እምነት ማውጫ መንገዶች ካልተጠቀሙና ጭጭ ብለው ከተቀመጡ አንዳች መልካም ነገር እንደማያስገኝ ያረጋግጣል፡፡

ዕብ 11 የእግዚአብሔር ሰዎች በነበራቸው እምነት የተለያየ ድርጊት ስለ ፈጸሙ ስኬታማ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ አቤል መስዋዕተን በእምነት ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ሄኖክ በእምነት ሞትን አላይም ብሎ ተናገረ፤ ኖህ በእምነት መርከብን ሰራ፣ አብርሃም በእምነት ወደ ማያውቀው አገር እግዚአብሔርን እሺ ብሎ ተጓዘ፤ ወደ ከነዓናውያን ምድር እንደ ደረሰ እግዚአብሔር በነገረው ቃል መሰረት በእምነት ተቀመጠ፤ ...

12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት እንዳደረገችው የእግዚአብሔር አገልጋይ ልብስ ብነካ እፈወሳለሁ ብሎ በማመን የእግዚአብሔር አገልጋይን ልብስ ከእርሷ በፊት መንካቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ምሳሌ ስላገኘች ሳይሆን እርሷ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን አሰራር በልቧ ስለ መጣላት ነው የተጠቀመችው፡፡

ስለዚህ ከላይ በቃሉ የሰፈሩት እንዲሁም በአሁኑም ጊዜ አማኞች የታማሚው ፎቶ፣ ካናቴራ፣ ወይም ዘይት፣ እንደ ገጠማቸው የተለያየ ጉዳይ ማንኛውም ጸያፍ ያልሆነ/ከኃጢአት ጋር ንክኪ የሌለው ነገር አገልጋዩ ወይም ተገልጋዩ በልቡ እንደመጣለት መርጦ እምነትን ስራ ላይ ለማዋል መጠቀም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ ያለና የሚደገፍና ተገቢ ነገር ስለሆነ፣

ማንኛውም አማኝ/አገልጋይ ይህን ዓይነት ድርጊት በመጠቀሙ/በማድረጉ የሚነቀፍበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባም፡፡ ይህን ለምን አደረጋችሁ ብለው አገልጋዮችንም ሆነ ምዕመናንን ለሚነቅፉ ሰዎች፣ መፍትሔው እግዚአብሔር የሚፈቅደው መንፈሳዊ እውነትን አውቀው ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆኑ/ከፈለጉ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ወይም መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ መምከር ነው፡፡

ሌላው ሁሉም ሊረዳው የሚገባ ነገር በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ቁሳቁሶች ውስጥ ሰውን የሚፈውስ ወይም የተፈለገው መልካም ውጤት የሚያስገኝ ምንም ኃይል የሌለና ኃይሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚመጣ መሆኑን፣ ቁሳቁሶቹ ሁል ጊዜ እቤታችን አጠገባችን የነበሩ ወይም ያሉና የሚኖሩ፤ ግን እኛ ያስፈለገን ወይም የምንፈልገው ነገር የሚያስገኝ ኃይል በውስጣቸው ያልነበረ ወይም የማይኖር መሆኑን በማወቅ በቁሳቁሶች ወደ ማመን ማዘንበል እንዳይሆን መጠንቀቅ ነው፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.